**በጉምሩክ ኮሚሽን**
**የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት**
**CUSTOMS COMMISSION**
**ADDIS ABABA KALITI CUSTOMS BRANCH OFFICE**
**የሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት የውስጥ ማስታወሻ**

ቁጥር፡ ስ/አ/ጽ/ቤት 52/12
ቀን: 08/03/2012 ዓ.ም

ለ፦ ንግድ ገቢ ዕቃዎች አወጣጥ የስራ ሂደት
ለ፦ ወጪና ንግድ ያልሆኑ ገቢ ዕቃዎች አወጣጥ የስራ ሂደት
ለ፦ ኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት
ለ፦ ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት
ለ፦ ገላን ጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ
ለ፦ እንዶዴ ባቡር ጣቢያ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት
ለ፦ ትራዚትና መጋዘን አስተዳደር የስራ ሂደት
ለ፦ የተተዉና የተወረሱ መጋዘን አስተዳደር የስራ ሂደት

ከ፦ ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
ቃ.ቃ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ጉዳዩ፦ ዕቃዎች በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ የሚቆዩበት ጊዜ ይመለከታል፤

የጉምሩክ ኮሚሽን በቁጥር 4/03/0/12 በቀን 02/03/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀጽ 13(11) ኮሚሽኑ በአዋጁ የተወሰኑ የጊዜ ገደቦችን በበቂ ምክንያት ሊያራዝም እንደሚችል በተደነገገው መሰረት፦

1. የኮሚሽኑ ደብዳቤው ወጪ ከሆነበት ከህዳር 2, 2012 ዓ.ም በፊት ተጓጉዘው ደረቅ ወደብ በመግባት የትራንዚት ሂደታቸውን ያጠናቀቁ ጭነቶች እስከ ህዳር 30/2012 ዓ.ም ደረስ ያለቅጣት አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ተፈጽሞባቸው እንዲስተናገዱ እንዲደረግ፤
2. የኮሚሽኑ ደብዳቤ ወጪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ተጓጉዘው ወደ ደረቅ ወደብ በመድረስ ትራንዚት የሚያጠናቅቁ ጭነቶችን በሚመለከት በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀጽ 13(1) እና (2) በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተገቢው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈጽሞባቸው እንዲስተናገዱ እንዲደረግ፤ ስለአፈጻጸሙ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ እንድናሳውቅ፣ ስለ አፈጻጸሙ በየደረጃው ጥብቅ ክትትል እንዲደረግ እና በዚሁ አግባብ አገልግሎት የተሰጣቸውን ዝርዝር መረጃ ሪፖርት እንድናቀርብ አሳስቦናል፡፡

ስለሆነም በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት በጥብቅ እንዲፈጸም እያሳሰብኩ በዚሁ አግባብ አገልግሎት የተሰጠባቸውን ዝርዝር መረጃ ሪፖርት በሚመለከታቸው ዘርፎች በቅ/ጽ/ቤቱ የፕላንና የለውጥ ስራዎች ቡድን እንዲተላለፍና በቡድኑ በኩል ለኮሚሽኑ ሪፖርት እንዲደረግ እና የደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ የስራ ሂደትም አስመጪዎችና የጉምሩክ አስተላላፊዎች በተገቢው እንዲያውቁት እንዲያደርግ እያሳሰብኩ ከኮሚሽኑ የተሰጠውን አቅጣጫ 2 ገጽ ኮፒ ለአፈጻጸም ይረዳችሁ ዘንድ አባሪ በማድረግ ልከናል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ
ለ፦ ም/ስራ አስኪያጅ (አምራች ወጪና ሌሎች ጣቢያዎች)
ለ፦ ም/ስራ አስኪያጅ (የንግድ ገቢ ዕቃዎች ኦፕሬሽን)
ለ፦ ም/ስራ አስኪያጅ (ህግ ተገዥነት)
ለ፦ ም/ስራ አስኪያጅ (አቅምና ድጋፍ)
ለ፦ ደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ የስራ ሂደት
ለ፦ ፕላንና ለውጥ ሥራዎች ቡድን
ቃ.ቃ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቀን ሕዳር 02 2012
Date
ቁጥር 4/03/07/12
Ref.No.

**የጉምሩክ ስነስርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ**

**ባሉበት**

ጉዳዩ:- ዕቃዎች በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ስለሚቆዩበት ጊዜ ይመለከታል፡፡

የጉምሩክ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 ፀድቆ ሥራ ላይ መዋሉ ይታወቃል፡፡ በማሻሻያ አዋጁ አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ (1) "ማናቸውም በባህር ወይም በየብስ ተጓጉዞ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በ15 (አሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ተፈፅሞበት ከማከማቻው መውጣት እንዳለበት"፤ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) "ማናቸውም በአየር ተጓጉዞ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በ10 (አስር) ቀናት ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ተፈፅሞበት ከማከማቻው መውጣት እንዳለበት" ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ የማሻሻያ አዋጁ ከመፅደቁ በፊት እና ከፀደቀ በኋላ በመልቲ ሞዳል ሥርዓት ተጓጉዘው በጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች የደረሱ ዕቃዎች አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ተፈፅሞባቸው እንዲወጡ ለዕቃዎች ባለቤቶች የተደረገው የማሣወቅ እና ቅስቀሳ ሥራ በቂ አለመሆኑ ታምኖበታል፡፡

ስለሆነም በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ (11) ኮሚሽኑ በአዋጁ የተወሰኑ የጊዜ ገደቦችን በበቂ ምክንያት ሊያራዝም እንደሚችል በተደነገገው መሠረት:-



☎ +251 116 62 98 00
Fax +251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

1. ይህ ደብዳቤ ወጪ ከሆነበት ቀን በፊት ተጓጉዘው ደረቅ ወደብ በመግባት የትራንዚት ሂደታቸውን ያጠናቀቁ ጭነቶች እስከ ህዳር 30/2012 ዓ.ም. ድረስ ያለቅጣት አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ተፈፅሞባቸው እንዲስተናገዱ እንዲደረግ፣
2. ይህ ደብዳቤ ወጪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ተጓጉዘው ወደ ደረቅ ወደብ በመድረስ ትራንዚት የሚያጠናቅቁ ጭነቶችን በሚመለከት በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀፅ 13 (1) እና (2) በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተገቢው የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ተፈፅሞባቸው እንዲስተናገዱ እንዲደረግ እያሳሰብኩ፤ ስለ አፈፃፀሙ ለሚመለከታቸው አካላት በሙሉ እንድታሳውቁ ሆኖ በገቢ ዕቃዎች ላይ የጉምሩክ አገልግሎት አሰጣጡ ከላይ በተወሰነው አግባብ ተፈፃሚ እንዲደረግ ጥብቅ ክትትል እንድታደርጉና በዚሁ መሠረት የሰጣችሁትን አገልግሎት ዝርዝር መረጃ ሪፖርት ለኮሚሽኑ እንድታቀርቡ በጥብቅ አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

Federal Democratic Republic of Ethiopia Customs Commission No.2

ግልባጭ/
- ለጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለጉምሩክ ህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
  ጉምሩክ ኮሚሽን
- ለኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት
  አዲስ አበባ
- ለዕቃ አስተላላፊዎች ማህበር
- ለጉምሩክ አስተላላፊዎች ማህበር
  ባሉበት